

# በጾታዊ ትንኮሳ

# ተጽዕኖ ይደርስብወታል?

## መብትዎን ይወቁ።

በማንኛውም የትምህርት ቤት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት የተዘጋጁ የፊልድ ጉዞዎችና በመሳሰሉት የግቢ ውጭ  እንቅስቃሴዎች፣ ተማሪዎችና ሰራተኞች በማንኛውም ሰው ከሚደርስ ጾታዊ ትንኮሳ ጥበቃ ተደርጎላቸዋል።

## ጾታዊ ትንኮሳ ምንድን ነው?

የሚከተሉት  ድርጊቶች  ሲፈጸሙ ጾታዊ መልክ በአለው የማይፈለግ ባህሪ ወይም ግንኙነት ምክንያት ሲሆን ጾታዊ ትንኮሳ ይከሰታል ፦

- አንድ ተማሪ ወይም ሰራተኛ በምላሹ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ለምሳሌ የፈተና ውጤት፣ የስራ እድገት፣ በስፖርት ቡድን ውስጥ መመደብ፣ ወይም ሌላ ከትምህርት ወይም ከስራ ጋር የተገናኘ ጥቅም ለማግኘት ባልፈለገው/ቸው ጾታዊ ባህሪ ወይም ግንኙነቶች መሳተፍ እንዳለበት/ባት አድርጎ/ጋ እንዲያምን /እንድታምን ሲደረግ፣ ወይም
- ከተማሪው/ዋ የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳርፍ ወይም የሚያስፈራ ወይም የማይመች  የትምህርት ወይም የስራ አካባቢ የሚፈጥር ባህሪ ሲሆን።

## ጾታዊ ትንኮሳን እንዴት መጠቆም እችላለሁ?

ጾታዊ ትንኮሳን ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሰራተኛ ወይም ለዲስትሪክት ታይትል አይኤክስ ኦፊሰር መጠቆም ይችላሉ፦

*የእርስዎን ዲስትሪክት የጾታዊ ትንኮሳ ፖሊሲ እና መመሪያ ቅጂ ለማግኘት፣ ትምህርት ቤትዎን ወይም ዲስትሪክት ቢሮ ያነጋግሩ።*

## የጾታዊ ትንኮሳ ምሳሌዎች፦

- ለጾታዊ ጥያቄ መወትወት
- ያልተፈለገ ጾታዊ የሆነ የአካል ግንኙነት ማድረግ
- ጾታ ነክ የብልግና ጽሁፍ
- ጾታን የለየ አጭር ጽሁፎች፣ ኢሜሎች ወይም ስዕሎች ማሰራጨት
- ጾታ ነክ የሆኑ ቀልዶችን፣ ወሬዎችን፣ ምክር አዘል አስተያየቶችን ማቅረብ
- በሀይል መጠቀም፣ መድፈር እና ለወሲብ መያዝን ጨምሮ

**OSPI Equity and Civil Rights Office**
360.725.6162
equity@k12.wa.us
www.k12.wa.us/equity

Equal Access and Opportunities for Students and Educators
Equity & Civil Rights
PROMOTING EDUCATIONAL EXCELLENCE FOR ALL

SUPERINTENDENT OF PUBLIC INSTRUCTION WASHINGTON

OSPI እና የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ጾታን፣ ዘርን፣ ቀለምን፣እምነትን፣ ሀይማኖትን፣ የቀድሞ ሀገርን፣እድሜን፣ የአካል ጉዳትን፣ የጋብቻ ሁኔታን፣ ጾታዊ ዝንባሌን፣ የጾታ መለያን ወይም አገላለፅን፣ ዘማችነትን ወይም የውትድርና ሁኔታን ወይም የአካል ጉዳት በመኖሩ አጋዥ እንስሳት መጠቀምን መሰረት በማድረግ መድሎ አያደርግም፤ እንዲሁም  በወጣትነት የእድሜ ክልል ለሚገኙ በሙሉ አኩል ተደራሽነት መኖር አለበት። ጥያቄ ወይም ቅሬታ ካለዎት፣ ለትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎን ወይም  ለOSPI  ፍትሃዊነት እና ሲቪል መብቶች ቢሮ  በፖስታ P.O. Box 47200, Olympia, WA 98504 ወይም በስልክ  (360) 725-6162 ማድረስ ይችላሉ።

AMHARIC